# የበዕደ ማርያም ት/ቤት አመሠራረት፣ አስተዋጽኦና መዘጋት

ጋሻው አባተ

## መግቢያ

የበዕደማርያም የመሰናዶ ት/ቤት ታዋቂ ከነበሩት የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ እንደነበር ይነገራል:: የትምህርት ቤቱ መቋቋም ዋነኛ ዓላማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራንን በብቃት ለማሠልጠን ነበር:: ይህ የመሠናዶ ት/ቤት በዚያን ወቅት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በሚባለው ሥር ይተዳደር በነበረው በትምህርት ፋካልቲ ደጋፊነት እ.ኤ.አ በኦክቶበር 1962 ዓ.ም ተከፍቶ ከየሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በትምህርታቸው ብልጫ ያሳዩ ከነበሩት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የመመልመያ ፈተና በመስጠት እየመረጠ የአንድ አመት የ12ኛ ክፍል ትምህርትና ከዚያም የ4 ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርት በመስጠት እያስመረቀ ብቁ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራንን በማፍራት ጉልህ ሚና ተጫውቷል:: ት/ቤቱ በተለያዩ ችግሮች በብዛት የማሰልጠን አቅሙን አጎልብቶ የአገሪቱን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራንን ፍላጎት በቁጥር ማሟላት ባይችልም፣ በሚያሠለጥናቸው መምህራን ጥራትና ብቃት ግን ፍፅም የሚታማ አልነበረም:: እንዲያውም በአገሪቱ የትምህርት ታሪክ ጉልህ ሚና ይጫወቱ የነበሩና አሁንም ብቃታቸው የሚነገርላቸው ባለሙያዎች የዚሁ ት/ቤት ውጤቶች መሆናቸው ይወሳል::

ይሁንና ይህ ለዩኒቨርሲቲው የዕው መምህራን ዋነኛ ምንጭ ሆኖ ሲያገለግል የነበረ ተቋም ጠለቅ ያለ ጥናት ሳይደረግበት እ.ኤ.አ ከ1979 ዓ.ም ጀምሮ እንዲዘጋ ተደርጓል:: በሌላ በኩል ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና ችግር በየጊዜው እየተባባሰ ቆይቶ በአሁኑ ጊዜ አንገብጋቢነቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል:: አንዳንድ ምሁራንም እንደ ልዑል በዕደማርያም መታሰቢያ ት/ቤት ዓይነት እንደገና መፈጠር አለበት ይላሉ:: ጉዳዩ በደፈና መቀከር የሌለበትና ጠለቅ ያለ ጥናት የሚያስፈልገው ሲሆን ለአጀማመር ያመች ዘንድ የትምህርት ቤቱን አጭር ታሪክና አስተዋጽኦ በመጠኑ ለመቃኘት ተሞክሯል::

## የጥናቱ ዓለማና አስፈላጊነት

ይህ አጭር ጥናት የተከናወነው የሚ፣ተሉትን ዓላማዎች ገንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው::

ሀ/ የት/ቤቱን አመሠራረት፣ አስተዋጽኦና መዘጋት የሚያመለከቱ የተቀነባበሩ መረጃዎች ስለሌሉ ለማሰባሰብ

ለ/ በት/ቤቱ ላይና በተመሳሳይ መስክ ጥናት ለማድረግ ለሚሹ ተመራማሪዎች መነሻ የሚሆን ጽሑፍ ለማዘጋጀት

ሐ/ ስለ ት/ቤቱ አጠቃላይ ታሪክ ገንዛቤ ለማስጨበጥ::

## የጥናቱ ስልት

ጥናቱ የተካሄደው የጽሑፍ መረጃዎችን ከተለያዩ ቢሮዎች በማሰባሰብና ስለ ት/ቤቱ ያውቃሉ ከተባሉ ሰዎች በተገኘ የቃለ መጠይቅና የመጠይቅ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ነው:: መረጃ የሰጡት ሰዎች በትምህርት ቤቱ መምህራን የነበሩ፣ በት/ቤቱ በአስተዳደር ዘርፍ ሲሠሩ የነበሩና ከትምህርት ቤቱ ተመርቀው አሁን በተለያዩ የሀላፊነት ቦታ ላይ የሚያገለግሉ ስለሆኑ የተገኘው መረጃ ዐውነተኛነቱ የሚያጠራጥር አይደለም ተብሎ ይገመታል::

## ከጥናቱ የተገኙ ዘገባዎች

ከጥናቱ የተገኙትን መረጃዎች በሁለት ዋና ዋና ርዕሶች ሥር ለማቅረብ ይቻላል::

1. ከጽሑፍ መረጃዎች የተገኙ
2. ከመጠይቅና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ ::

### ሀ. ከጽሑፍ የተገኙ መረጃዎች

በዚህ ጥናት በበዕደማርያም ላይና ስለበዕደማርያም ትምህርት ቤት መዘጋት መጣጥፎችን በመዳሰስ በመረጃነት ይረዳሉ የተባሉ ሀሳቦች ተወስደዋል::

## የልዑል በዕደ ማርያም የመሰናዶ ትምህርት ቤት አመሰራረት፣

ከነፃነት በኋላ ጦርነቱ አስከትሎት ከነበረው ሁለንተናዊ መዛባት ለማገገምና የወቅቱም የአለም አቀፍ "የስልጣኔ ደረጃ" የጠየቀውን መሰረት ለማሟላት እንዲቻል ዘርፈ ብዙና ጥልቅ የሆነ ጥረት በአገሪቱ ውስጥ ተጀምሮ እንደነበር የሚጠቁሙ መረጃዎች አልታጡም:: የጥረት አቅጣጫው ካተኮረባቸው ዘርፎች ውስጥ የትምህርቱ ጉዳይ ይገኝበታል:: በትምህርቱ ዘርፍ ላይ ያተኮረው ትኩረት በተለይ ከ1950 /እ.ኤ.አ/ ወዲህ እንደበረታም ይነገራል:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከ 1962 /እ.ኤ.አ/ ባለው ዘመን ውስጥ አያሌ ጉዳዮች ተከናውነዋል:: የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ይባል የነበረው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የሆነውም በጃንዋሪ 1962 /እ.ኤ.አ/ ነበር:: በ1952 /እ.ኤ.አ/ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ማሰልጠኛ የነበረው "ሴክሽን" ወደ የትምህርት ክፍል / Department / ያደገው በ1959 /እ.ኤ.አ/ ሲሆን ይኸው ሂደት ሳይገታ የትምህርት ክፍሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የነበረው ከላይ እንደተጠቀሰው ወደ ዩኒቨርሲቲነት ከፍ ሲል የትምህርት ክፍሉም "የትምህርት ፋክልቲ" ተብሎ አደገ ::[1]

በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ የታየ እንደሆነ የልዑል በዕደ ማርያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ማሰልጠኛ የመሰናዶ ትምህርት ቤት አከፋፈትም የዚሁ ሂደት አካል መሆኑን መረዳት ያሻል:: ትምህርት ቤቱ ለራስና በራሱ ምክንያት ብቁ ያለ አይደለም::

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ እንደተከፈተ ማለትም /እ.ኤ.አ/ በ1962 የአሜሪካ የአለም አቀፍ እድገት ወኪል / USAID / ከኡታህ ዩኒቨርስቲ ጋር ኮንትራት ተፈራረሙ:: የኮንትራቱ አላማ የኡታህ ዩኒቨርሲቲ አንዱ የባለሙያዎች ቲም ወደ ኢትዮጵያ በመላክ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲን የትምህርት ፋኩልቲ እንዲት ማቋቋምና ማደራጀት እንደሚቻል እንዲረዳ ለማድረግ ነበር:: ወቅቱም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን በእጅጉ የተፈለገበትና ነገር ግን የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን / ESLCE / ከሚያልፉት እጅግ ጥቂት ተማሪዎች መካከል ወደ ትምህርት ፋኩልቲው ለመግባት ፍላጎት የነበራቸው

በአንፃራዊ አነጋገር ያልነበረበት ወቅት ነበር:: የትምህርት ፋኩልቲው ደግሞ ድርጅታዊ ብቃቱንም አሟልቶ ብቃት ያላቸው መምህራኑን ይዞ ለመሰልጠን የሚፈልጉ ተማሪዎችን የሚጠባበቅበት ዘመን ነበር::[2] በአንዱ ዓመታዊ የት/ቤት ሪፖርት ውስጥ እንደተዘገበው ከሆነ፣

> A major problem was discovered as the newly established Faculty of Education found itself with a program and qualified teachers, but with out sufficient students. It was soon learned that only a few students, relatively speaking, could even qualify for the university through the regular avenue, the ESLCE, of those few qualifying students almost no one chose[3] to join the Faculty of Education.

ከአሜሪካ የተላከው አጥኚ ቡድን በትምህርት ፋኩልቲ ሰልጣኝ ተማሪ ያለመገኘቱ መፍትሄ የሚያሻው ችግር ሆነበት:: መፍትሄ ይሆናሉ የተባሉ አማራጮች ሁሉ ታዩ::

የ12ኛ ክፍልን መልቀቂያ ፈተና በማለፍ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከሚደርሱት ተማሪዎች ሌላ በእርግጥ ብቁ የሆኑ ሌሎች ተማሪዎች ማግኘት እንደሚቻል በሃሳብ ደረጃ ተደረሰ:: ከ10ኛና 11ኛ ክፍሎች መልምለው የተለየ ስልጠናና የ12ኛ ክፍሉን ካሪኩለም ትምህርት በማጣመር አጠር ቱ ውጤት አገኙ የተባሉት እንደባህር ኃይል አየር ኃይልና የመሳሰሉት ድርጅቶች ለዚሁ በማስረጃነት ይረዱ ዘንድ ተዘገቡ:: የዚህ ዓይነቱ የምክንያት አደራደር አይቀሬ መዳረሻ የዩኒቨርሲቲው ለምን እንዲህ አያደርግም ወደሚለው ሆነ::[4] ቀጥሎ የተነሳው ጥያቄ ደግሞ እንዲህ ተመልምሎ የተገኙት ተማሪዎች የት ሆነው ይሰልጥኑ የሚል ነበር መልሱም እንደሚከተለው ሆኖ ቀረበ::

> other proselyting programs all offered completion of secondary school programs along with specialized training. The Laboratory School seemed the builtin answer.[5]

በመጨረሻም ቱው የአስተያየት /Recommendations/ በነዱ አዘጋጀ:: ከአስተያየቶቹ መካከል የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና የመሰናዶ ትምህርት ቤት መከፈት የሚል ይገኝበታል:: የመሰናዶው ትምህርት ቤት የተሰፋፋ የ12ኛ ክፍል ፕሮግራም ሆኖ ከዩኒቨርስቲው እንዲጨመር ተበየነ:: ተማሪዎቹ በሀገሪቱ ከሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በትምህርታቸው ቀደምትነት ካላቸው ውስጥ በተለየ የመመዘኛ ፈተና ተጨርተው የሚመለመሉ ሲሆኑ፣ በዩኒቨርስቲው ውስጥ በሚገኘው ከሳይ በተጠቀሰው ፕሮግራም ለአንድ ዓመት በመቆየት ለወደፊት በዩኒቨርሲቲው ለሚያጋጥማቸው የመምህርነት ስልጠና የመሰናዶ ዝግጅት የሚያደርጉ ናቸው:: ወደ ተባለው ፕሮግራም ተማሪዎችን ለማምጣት የሚረዱ ተጨማሪ መስህቦች /inducements/ ተዘጋጁ:: ከነዚያም መካከል ወደ ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ፋኩልቲ ለመግባት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና መውሰድ ሳያስፈልግ በትምህርት ቤቱ አስተያየት /Recommendation/ ብቻ እንደ ሚቻል የሚደነግገው ይገኝበታል::[6]

በወቅቱ የተከሰቱት ችግሮች ብዛታቸው እና እነርሱንም ለመቅረፍ በተደረገው ሙከራ ጥናትና የጥናት ግኝት ሳቢያ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ በትምህርት ፋኩልቲ ደጋፊነት /Sponsor/እና ከኮታህ ሆ አንጉ በነበረት በደ/ር ጃክብሰን መሪነት ኦክተበር 1962 /እ.ኤ.አ/ የልዑል በዕደ ማርያም የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና መሰናዶ ትምህርት ቤት ተከፈተ:: በየዓመቱም 150 ተማሪዎች እየወሰደ እንዲያሰለጥን ሆኖ ሥራውን ጀመረ::

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሁለት መሰረታዊ ፕሮግራሞች ነበሩ:: እነርሱም ልዩ የ12ኛክፍል እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞች ናቸው:: ልዩ የ12ኛ ክፍል ፕሮግራም / Special Grade 12 Program / በአገሪቱ ከሚገኙት ከፍተኛ ውጤት ካላቸው የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የተለየ የመመዘኛ ፈተና በመስጠት መልምሎ ሥራውን የሚጀምር ፕሮግራም ነበር:: የመቀበል ችሎታው በዓመት ከ150 ተማሪዎች እንደማይበልጥ ቢደነገግም ቀጥረን በመጨመር ከ150 ተማሪዎች በላይ ያስተናገደባቸው ዓመታት እንደነበሩ ይታወቃል::

ለቁ የ12ኛ ክፍል ፕሮግራም በዲፓርትመንቶቹ ተከፋፍሎ እያንዳንዱ በአንዱ የዲፓርትመንት ኃላፊ እንዲመራ ሆኖ የተደራጀ ነበር:: እያንዳንዱ የክፍል ኃላፊ ለክፍሉ የትምህርት ዓይነቶች የመማር ማስተማር ሂደትና በሚቀጥለው ዓመት ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡት ተማሪዎች በበቂ መዘጋጀታቸውን የመከታተል፣ የትምህርት ክፍሎችን የማዋቀር፣ የመምራት፣ ሳምንታዊ ስብሰባዎችን የማካሄድ፣ ከሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ ዘርፍ ትምህርት ወይም ፋኩልቲ ጋር እንደአስፈላጊነቱ ቅርብ ግንኙነትን የማድረግ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ዓመታዊ የትምህርት እቅድ ሲነድፍ የመተባበር ኃላፊነት እንዲኖረው ተደርጎ የተሰየመ ትምህርት ክፍል መሪ ነበር::

ተማሪዎቹ በትምህርት ቤቱ ርዕሠ መምህርም ሆነ በመምህራኑ ጥብቅ ክትትልና ዕርዳታ ይደረግላቸው ስለነበር የትምህርት ውጤታቸው አጥጋቢ ነበር:: ለምሳሌ ያህል የት/ቤቱ ተማሪዎች በ1970 ዓ.ም በ ESLCE ያመጡትን አማካይ ውጤትና በዚያው አመት የመሰናዶውን ት/ቤት የትምህርት መርሀ ግብር አጠናቀው ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ የተፈቀደላቸውን ተማሪዎች የሚያሳዩ ሁለት ሠንጠረዦች ለአብነት ቀርበዋል::

ሠንጠረዥ 1

በ1970 ዓ.ም በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የበዕደ ማርያም ተማሪዎች የፈተና ውጤት

| ውጤት | A | B | C | D |
|---|---|---|---|---|
| ውጤቱ የተገኘበት መጠን | 45 | 88 | 79 | 22 |

ምንጭ: HIU, Prince Bede Mariam Lab. School, Director's Report for the School Year, 1969-70.

ሠንጠረዥ 2

በ1970 ዓ.ም ከት/ቤቱ ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ የተመረጡ ተማሪዎች

| ክፍል | ወደ ዩኒቨርሲቲ ሂያጆች | ወደ ዩኒቨርሲቲ አይሄዱም የተባሉት | ድምር በየክፍሉ |
|---|---|---|---|
| /አርትስ/ | 24 | 7/2= የተባረሩ | 33 |
| /ሳይንስ/ | | | |
| /አርትስ/ | 24 | 7 | 31 |
| አርትስ | 23 | 6/1= የተባረሩ | 30 |
| አርትስ | 28 | 7 | 35 |
| ሳይንስ | 30 | 1 | 31 |
| " | 24 | 5 | 29 |
| " | 28 | 5 | 33 |
| " | 22 | 14 | 36 |
| ድምር | 203 | 52/3 | 258 |

ምንጭ:

HIU, Prince Bede Mariam Lab. School Director's Report for the School Year 1969-70.

ተማሪዎቹ ወደ ዩኒቨርሲቲው ከገቡ በኋላ የሚያሳዩት ትጋትና የትምህርት ውጤት አመርቂ እንደነበር ብዙ ተዘግቧል:: በቁጥር ብዙ አይሁኑ እንጂ ምሩቃኑም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራንን እጥረት ችግር ለመቅረፍ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

የበዐደማር ያም የመሰናዶ ት/ቤት ለሁለተኛ ደረጃ መምህራን ዝግጅት ያደረገውን አስተዋጽኦ ለመገንዘብ የሚከተለውን ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ 3፡

1969-74 /እ.ኤ.አ/ በትምህርት ፋኩልቲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምሩቅ መምህራንና በትምህርት ሚኒስቴር በእውን የነበረት መምህራን ቁጥር የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡፡

| ዘመን | የምሩቃኑ ቁጥር | በትምህርት ሚኒስቴር የነበሩ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን | የምሩቃን % |
|---|---|---|---|
| 1969 | 44 | 4022 | 1.09 |
| 1970 | 77 | 2347 | 3.28 |
| 1971 | 68 | 3864 | 1.76 |
| 1972 | 65 | 4645 | 1.40 |
| 1973 | 74 | 4819 | 1.54 |
| ድምር | 328 | 19697 | 1.67 |

ምንጭ፡

ትምህርት ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርትና ሥልጠና ጥናታዊ ግምገማ 1983 ዓ.ም

"መገለጫ" በሚል ስያሜ ይታተም በነበረው የበዐደ ማርያም ትምህርት ቤት መጽሔት " የኢትዮጵያ መሰናዶ ትምህርት ቤት፣ ክንዋኔና የወደፊት አሳማያች" በሚል ርዕስ ሥር ረይቲ ዊልክከስ የትምህርት ቤቱን የእድገት ደረጃዎች፣ ትምህርት ቤቱን ለመክፈት ያበቁት የመንደርደሪያ አሳማያች በወቅቱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን እጥረትና በሂደት ያጋጠሙ ተጓዳኝ ችግሮች የተመዘገቡ ግንቶችንና የእፄ በዐደማርያም ት/ቤት የወደፊት እድል በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች ሥር አያሌ ጉዳዩችን ዘርዝረዋል፡፡

በአጠቃላይ ገጽታው ሲታይ ግን 'ጸሐፊው ባንድ በኩል ትምህርት ቤቱ በአሰለጣጠን ለመቋቋም ወደረገ ከነበረበት እርምጃ አንፃ ጥው ይህ ዓይነቱን ትምህርት ቤት መከፈት እንደነበር ሲገለጹ በሌላ በኩል ግን ትምህርት ቤቱ እንዱ ቀን ሊዘጋ እንደሚችል የሚጠቁሙ ሁኔታዎች እንደነበሩ ይናገራሉ::

> There has been talk of the Ministry of Education forbidding all recruiting of students from the Public Schools until after twelvth grade. If such a rule were made and enforced, the Laboratory School along with other organizations could no longer take students from the public schools as they are now doing. In such a circumstance, the recruitment function of the present Laboratory School would be obsolete. It has also been proposed that the Ethiopian Government should, with the help of outside agencies, establish schools of the Junior College type to train its needed Secondary School Teachers.

ፀሐፊው ከላይ ከተጠቀሰው የትምህርት ሚኒስትር ውሳኔ ሊሆን ይችላል ተብሎ ከተገመተው አዝማሚያ በመነሳት የበዐደማርያም መሰናዶ ት/ቤት ህልውናና ተማሪዎችን መመልመል መቻል ወይም አለመቻል የቱን ያህል የተቀራኙ ስለመሆናቸው እንዲህ ይላሉ::

> ...Of course, the author is speculating but it does appear that there are strong possibilities that the laboratory school might loose its recruitment function, one of its main reasons for being. In such a situation, the laboratory school could not justify its continuance simply to handle observers from the Faculty of Education or to help provide student teaching.

በመጨረሻም የመሰናዶው ትምህርት ቤት ተዘግቶ ሥራውን አቋርጧል::

በቅርቡ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠናን በተመለከተ ካለው ችግር ለመላቀቅ የሚያስችሉ መፍትሔዎችን ለመሻት ልዩ ልዩ የጥናት ቡድኖች ያቀረቧቸው ሀሳቦች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ያህል ጥቂቶቹ ቀርበዋል፡፡

1. የኢትዮጵያ የትምህርት አጠቃላይ ጥናት /Sector Review/ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠናን በገመገመበት ክፍሉ ከበዐደ ማርያም መሰናዶ ትምህርት ቤት የተመረቁት መምህራን የአካዳሚክ ብቃታቸው አጠያያቂ ባይሆንም ወጠናቸውና ስለመምህርነት ሙያ የነበራቸው ፍቅር እጅግ አጠያያቂ እንደነበር ጠቁሟል፡፡ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣው የተማሪዎች ቁጥርና በማይመጣጠን ደረጃ የማያድገው የመምህራን ቁጥር ንጽጽር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ችግሩን እንደሚጠቁም ጥናቱ አመልክቷል፤ ለምሳሌ እ.ኤ.አ ከ1962-63 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር 34,000 እንደሚደርስና 1,423 ተጨማሪ መምህራንም እንደሚያስፈልጉ ተገምቶ እንደነበር፤ ነገር ግን የበዐደማርያም ትምህርት ቤት በ1963 ለማሰልጠን የተቀበለው 150 ተማሪዎችን ብቻ እንደነበር ጥናቱ ያሳያል፡፡[7]

2. በተጨማሪም የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርትንና ስልጠናን የገመገመው የ1983 የትምህርት ሚኒስቴር ጥናታዊ ግምገማ የሚከተለውን የመደምደሚያ ሀሳብ ዘግቧል፡፡

> በተለያዩ ጥናቶች ግምገማዎችና ሪፖርቶች ስለሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና የቀረቡ ቢሆንም በጣም ጠቃሚና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የአጭርና የረጅም ጊዜ መፍትሄዎች ቢሰጡም ከፋይል አልፈው ችግሩን አላቃለሉም፡፡ የሚወሰዱትም እርምጃዎች የዘላቂነት ወይም የተከታታይነት ጠባይ የላቸውም፡፡ በግብታዊነት የሚካሄዱ በመሆኑ ተመራቂዎቹም ክህሎት የጎደላቸው የመንፈስ ዝግጅት ያላደረጉ በራሳቸው የማይተማመኑ ለሙያ ቃለ-ገብነት /commitment/ የሌላቸው ለሁለገብነት የሰለጠኑ ለአንድም ሙያ ያልበቁ በየዓመቱ በተገኘ ቀዳዳ በመጠቀም ሙያውን ጥለው የሚፈረጥጡ የቀጣሪያቸውንም ሆነ የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት የማያረኩ ናቸው፡፡[8]

ከዚህ ወደምደሚያ በመነሳት የመፍትሄ ሀሳቦችን ሲያቀርብ የእው መምህራንን ምልመላ በተመለከተ አማራጭ አራት ተብሎ የሚከተለውን አቀርቦ ነበር::

> ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መካከል 11ኛ
> ክፍልን ሲያጠናቅቁ ከፍተኛ የትምህርት
> ውጤት ያላቸውን መርጦ የአንድ ዓመት
> የመሰናዶ ትምህርት ቤት ከፍቶ በማስተማር
> ወደ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ማሰልጠኛ
> ተቋም ማስገባት::9

3. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና ያለበትን ሁኔታ ገልጸው ችግሩን ለመቅረፍ ይበጃሉ የተባሉ ሀሳቦችን ለትምህርት ሚኒስትር በደብዳቤ እንደሚከተለው ገልጸው ነበር::

> ... የትምህርት ቤቶች ቅኝት እየተደረገ
> በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት ያላቸውንና
> ለመምህርነት ሙያ ዝንባሌ ያላቸውን ከ11ኛ
> ክፍል መልምሎ በመሰናዶ ትምህርት ቤት
> አቆይቶ ማስገባት::10

4. ከትምህርት ሚኒስቴርና ከከፍተኛ ትምህርት ዋና መምሪያ ከተውጣጡ አባላት የተመሰረተ አንድ ኮሚቴ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እንዳሉት በጥናቱ ሪፖርት አማራጭ ሶስት የሚከተለውን አቀርቧል::

> ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ከሙያ ትምህርት
> ቤቶች የ11ኛን ክፍል ትምህርት ካጠናቀ
> ቁት ተማሪዎች መካከል በትምህርታቸው
> ከፍተኛ ውጤት ካላቸውና ለመምህርነት ሙያ
> ዝንባሌ ካሳዩት መካከል መርጦ የ6 ወር
> የዝግጅት ትምህርት ከሰጥቷቸው በውጤታቸ
> ውና በዝንባሌአቸው መሠረት በየትምህርት
> አይነቱ እንዲሰለጥኑ ወደለደል::11

ባጠቃላይ የተዘጋጁ ጽሁፎች ዳሰሳው አበይት ጉዳዮች ገለጻ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚከተሉት ነጥቦች ለማጠቃለያ ያህል ቀርበዋል::

1ኛ/ የበዐደማርያም የመሰናዶ ትምህርት ቤት በአወቃቀሩ፣ አደረጃጀቱ፣ አስለጣጠኑና አመራሩ አጅግ ብቁ ነበር::

2ኛ/ በሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርት የግምገማ ጥናት ያደረጉት /መጠንና ጥራትን አስመልከቶ/ ሁሉ በአማራጭነት ካቀረቧቸው ወይም ከሚጠቁሟቸው ጉዳዮች መካከል የበዐደማርያም ዓይነት የመሰናዶ ትምህርት ቤት መከፈት አስፈላጊነት ይገኝበታል::

3ኛ/ የበዐደማርያም ትምህርት ቤት የመምህራን አጥረቱን ለመቀነስ የቱን ያህል እንደረዳ በግልጽና በስፋት የመረመረ ጽሁፍ ወይም ጥረት የለም:: መረጃዎቹ በእጅ አዙር ዳሰሳ የሚያሳዩት ትምህርት ቤቱ የሚያስናዳው የተማሪ ቁጥርና ትምህርት ሚኒስትር የሚፈልገው የመምህር ዓይነት በአሀዝ አጅግ የሚቀራረቡ አይደሉም::

4ኛ/ የመሰናዶ ት/ቤት መኖር አለመኖር የሚጠቀሰው የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስልጠናን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲነሱ ነው:: ጥናቶቹ ሪፖርቶቹም የመምህራን የስልጠና ጥራት፣ የሰለጠኑ መምህራን ብቃት፣ የቅድመ ስልጠና ምልመላ፣ የመምህራን ደሞዝና መምህራንን በማስተማር ሙያ ማቆየትና የመሳሰሉት ጉዳዮች ምን ዓይነት ውስጠ-ተዛምዶ እንዳላቸው በግልጽ አሳባዎም:: የመምህራንን እጥረት ለማቃለል መፍትሄ ሲሰነዝር የመሰናዶ ትምህርት ቤት ላይ ማተኮር አይጠላም:: ሆኖም የተዘረዘሩት ጉዳዮችና የሚባለው ዓይነት ት/ቤቶች አወንታዊ መስተዓምራቸው መገናዘብ ይኖርበታል:: በአስፈላጊነታቸው ደግሞ ተዋረዳቸውን ማጤን ይገባል::

ከግኝቱ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ የበዐደማርያም ትምህርት ቤት የቱን ያህል በዕጩ መምህራን ምንጭነት ዩኒቨርሲቲውን እንዳገለገለ ታይቷል:: ለወደፊቱ ይከፈት ተብሎ ባማራጭነት የቀረበው ትምህርት ቤትም ከ10ኛና 11ኛ ክፍሎች ይመለመል ማለቱ ብቻውን በቂ አይደለም:: ባንዱ በኩል

የአሁኑ ዘመን 1ዐኛና የ11ኛ ክፍሎች የደረጃ ጥራት፣ በሌላ በኩል ብቃት ያላቸው ምልምሎች ባሉት ስንት ሊገኙ ይችላሉ፣ ባስፈላጊው መጠን ሊያሰለጥን የሚችል ት/ቤት መከፈት ይቻላልን ወዘተ... የመሳሰሉትን ጉዳዮች ያጤነ ጥናት ወይም ሪፖርት አልተገኘም:: መምህ ራንን መመልመልና የሚመለመሉበትን ምንጭ ለይቶ ማወቅ የመሰናዶ ትምህርት ቤት ይከፈት በሉ አማራጭ እንደማቀረብ ቀላል አይሆንም:: ጉዳዩ ግን አንገብጋቢ ስለሆነ በሚመለከተው በኩል አንድ መሥመር የሚይዝበትን መንገድ የሚጠቁም ጠለቅ ያለ የጥናት ውጤት ያስፈልገዋል::

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለመጠቃቀስ እንደተሞከረው የበዐደማርያም የመሰናዶ ት/ቤትን ሙሉ ሕይወት ጥርት ባለ መልኩ ለማቀረብ የሚያስችል የጽሑፍ መረጃ አልተገኘም:: ይህንን ለመጠገን ስለ ትምህርት ቤቱ የሚያውቁ ባለሙያዎችን በማነጋገር ከተገኘው የቃል መረጃ ቀንጨብ በማድረግ እንዲቀርብ ተደርጓል::

## ለ. <u>የመስክ ጥናት ግኝት</u>

በዚህ ክፍል ከሶስት ግለሰቦች ጋር የተካሄደውን ውይይት ውጤት ለማቅረብ ተሞክሯል::

### <u>ጥያቄና መልሶች</u>

<u>ጥያቄ 1</u> የበዐደማርያምን ትምህርት ቤት በአወቃቀሩ በአስተዳደሩ፣ በካሪኩለሙ በማሰልጠን ብቃቱና በመሳሰሉት እንዴት ይገመግሙታል?

<u>መልስ 1</u> አምሳያ አልነበረውም::

<u>መልስ 2</u> አጅግ አመርቂ ውጤት አሳይቷል::

<u>መልስ 3</u> በትምህርት ቤቱ ለመሰልጠን ፍላጎት ባይኖረኝም ት/ቤቱ በራሱ ሲታይ ግን አጅግ በጣም ጥሩ ት/ቤት ነበር::

ጥያቄ 2 የበዕደማር ያም ትምህርት ገና ከበፊቱ ሲከፈት ስለ ወደፊት ህይወቱ የተሰማዎት ነገር ነበር?

መልስ 1 የአሰራር ጥራቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ካፓሲቲውን አውቀው ስለነበር በጊዜው የነበረውንም ሆነ የተከታታይ ዓመታት የመምህራን ጥያቄ /Demand / ማሟላት እንደማ ይችሉና በዚሁ ምክንያት ሊዘጋ እንደሚችል ግምት ነበረኝ::

መልስ 2 እኔ ምንም ሀሳብ አልነበረኝም::

ጥያቄ 3 ወደ በዕደማር ያም ትምህርት ቤት ለመግባት ለምን ፈለጉ? በአርሶ ዘመን የነበሩ ተማሪዎችስ ለምን ወደ ት/ቤቱ የገቡ ይመስልዎታል?

መልስ 1 ፈልጌ እንኳን አልነበረም:: የ12ኛ ክፍል ፈተናን ድንገት ባሳልፍ አደጋ ለመቀነስ ነው የገባሁት:: የአስራ ሁለተኛ ክፍል ፈተናን ካለፍኩ ደግሞ 500.00 ብር ከፍዬ ፋኩልቲ መለወጥ እንደምችል አውቀው ነበር:: ሌሎች ተማሪዎች ግን የተለያዩ ምክንያቶች ነበሩአቸው:: ለምሳሌ አንዳንዶቹ እንደኔው ከአደጋ ለማምለጥ የገቡ ነበሩ:: ወደ አዲስ አበባ ለመግባት ብርቅ ሆኖበት የገባም አውቃለሁ:: የበዕደማር ያም ት/ቤት "የአምስት ዓመት ኮሌጅ" መሆኑን እንጂ ምን የሚሰራ ኮሌጅ እንደሆነ ባለማወቅ የገባ ጓደኛ ነበረኝ:: እንደሚታወቀው 12ኛ ክፍል ከባድ ዓመት ነው:: ለፈተና ከፍተኛ ዝግጅት የሚደረግበት:: ከገጠር ወደ ከተማ ስንቅ ለሳምንት እየተሸከሙ ይማሩ የነበሩ ልጆች እንደ ጥንቱ እየተመላለሱ ማጥናት ስለማይችሉ ካልተዘጋጁ እንወድ ቃለን ስለሚሉና ስንቅ አቅራቢም ስለማያገኙ ወደ በዕደማር ያም ት/ቤት መምጣቱ ጥሩ አማራጭ ሆነላቸው:: በእንዲህ ዓይነት ምክንያት የገባም አውቃለሁ:: ብቻ አስተማሪ ለመሆን ፈልጎ የገባ አላውቅም:: ቢገባም በዕደማር ያም ከገባ በኋላ የፍላጎት ለውጥ ያስከትላል::

**ጥያቄ 4** የበዐደማርያም የመሰናዶ ት/ቤት ወ ፰ እንዴትና ለምን
እንደ ተዘጋ ያውቃሉ?

**መልስ 1** ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ት/ቤቱ እንደሌለ አውቃለሁ::
አዘጋጉ እንዴት እንደ ተፈጸመ /የሴኔት፣ የት/ሚኒስቴር፣
የኘሬዚዳንቶች ወይም የመንግሥት ውሳኔ ይሁን አይሁን
አላውቅም/:: ከነዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም:: ከነዚህ
ጋር አብሮ ሊታይ የሚችል የተዘገበ ምክንያት አላውቅም::
ስገምት ግን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ከፍተኛ
የስልጣን ተሸካሚ /ኘሬዚዳንት፣ ም/ኘሬዚዳንት/ የነበሩት
አብዛኛው የትምህርት ፋኩልቲ መምህራን ነበሩ:: በመሆኑም
የሌሎች ፋኩልቲ አባላት የትምህርት ፋኩልቲ በዚህ ምክን
ያት "አብጠት" አለበት የሚል እምነት አሳብረው ነበር::
ለማቀዝቀዝ ተብሎ የተደረገ ይመስለኛል:: በኋላ የዩኒቨ
ርሲቲው ምክትል የትምህርት ኘሬዚዳንት ባወጡት ዲዛይን
አራቱ ሳይንሶች/ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ እና ሂሳብ/
እራሳቸውን ችለው በሳይንስ ፋኩልቲ የቋንቋዎች ኢንስቲ
ትዩት ለብቻው እንዲሆንና እንደ ሳይኮሎጂ ያለው ዲፓርት
መንት ወደ ሶሻል ሳይንስ ፋኩልቲ እንዲቀላቀልና የትምህ
ርት ፋኩልቲ ለእነዚህ ክፍሎች የጋራ ኮርሶችን እንዲያ
ስተምር ተደርጎ ተዋቀረ:: የአቤቱታ አቅራቢ ኮሚቴ
ተቋቁሞለት አቤት አለ:: ትምህርት ሚኒስቴር ጉዳዩን
አጥንቶ ፋኩልቲውን እንደገና ለማጠናከር የሚረዳ ሃሳብ
የሚያቀርብ ኮሚቴ ሰየመ:: በጥናቱ መሠረት እንደገና
ፋኩልቲው እንዲጠናከር ተወሰነ:: ሆኖም ግን ፋኩልቲው
ለማንሰራራት አልቻለም::

በሌላ በኩል በወቅቱ የፋኩልቲው ም/ዲን የነበሩት 19
ገጽ የጽሑፍ አቤቱታና ቅሬታ ለት/ሚኒስቴር አቅርበው
ነበር:: ይህ ደብዳቤ የት እንዳለ ማወቅ ያስቸግራል::

መለስ 2 ሥራውን ያቋመው ከ1970 ዓ.ም ወዲህ ነው:: የተዘጋውም በወቅቱ የዩኒቨርስቲው ምክትል የአካዳሚክ ፕሬዚዳንት በቻቸውን በእጅ በተጻፈ ባለ አራት መስመር ጽሁፍ መዘጋቱን ለት/ፋኩልቲ ያሳወቁበትን ማስታወሻ አስታውሳለሁ:: ት/ቤቱ የተዘጋበት ምክንያቶች አያሌ ናቸው:: የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን የአቀርቦትን ችግር ለማቃለል ት/ቤቱ አስተዋጽኦ ያድርግ እንጂ ችግሩን ለመቅረፍ አልረዳም:: የትምህርት ፋኩልቲ ሰዎች የዩኒቨርሲቲውን ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ መያዝም ሆ ለማስያዝ እና ፋኩልቲውን ለማዳከም እናም ት/ቤቱን ለመዝጋት ምክንያት ለመሆን ያነሰ አልነበረም:: አብዩት ፈነዳ:: በት/ቤቱ የአንደኛ ደረጃ ፕሮግራም ውስጥ ከሚማሩት ውስጥ የት/ቤቱ የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ልጆች ይገኙበት ነበር:: የሚማሩት በነፃ ስለነበር በኋላ የተማሪዎቹ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የገንዘብ ጫና እስከተለና ለወደፊቱ በነፃ እንደማያስተምር ት/ቤቱ ሲገልጽ ወላጆቻቸው ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አቤት አሉ:: "የጭቁን ሕዝብ ጥያቄ በመሆኑ" በት/ቤቱና በመንግሥት መካከል ሆ ተፈጠረ ይህም ት/ቤቱን ለመዝጋት የራሱ ድርሻ የነበረው ይመስለኛል::

በት/ቤቱ ውስጥ የነበሩት ኢትዮጵያውያን መምህራንና ሠራተኞች ት/ቤቱ አንድ ቀን እንደሚዘጋ ያውቁ ነበር ይመስለኛል:: ስለሆነም በዚህ አጋጣሚ እዚህ እና እዚያ በለው ት/ቤቱ ከነሠራተኞቹ ወደ ዩኒቨርስቲው እንደሚቀላቀል ገመቱ:: ሁኔታውን ካመቻቹ በኋላ የውስጥ ለውስጥ ትግሉን ቀጠሉበት ተካካሳቸው ተቀላቀሉ::

እነዚህም ጉዳዮች ተዳምረው ትምህርት ቤቱን ያዘጉ ይመስለኛል::

ጥያቄ 5 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ችግር ለመቅረፍ በዕደማርያምን የሚመስል ትምህርት ቤት አሁን ቢከፈት መፍትሔ የሚሆን ይመስልዎታል?

መልስ 1 ባማራጭ ደረጃ ሊቀርብ ይችላል:: የተሻሉ አማራጮች ግን አሉ:: ለምሳሌ አሁን ከሚገኙት የአንደኛ ደረጃ መምህራን መካከል የተለየ መመዘኛ የማዘጋጀትና ከ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ነጻ በማድረግ በዩኒቨርሲቲው ትምህርት ፋኩልቲ አማካይነት ቢሰለጥኑ የተሻለ መፍትሄ ይሆናል::

ጥቅምም አለው:: መምህራኑ ከመሰናዶ ት/ቤት የላቀ የተገባርና የቲዎሪ ዝግጅት ያላቸው ናቸው:: በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚሰለጥኑበት ወቅትም ብዙ ላያስቸግሩ ይችላሉ:: ዋናው ግን ለአንደኛ ደረጃ መምህራን ገራም የሆነ የእድገት በር ይከፍታል:: መስህብ /incentive/ ነው::

መልስ 2 የትምህርት ሚኒስቴርን ጥያቄ ማሟላት እንዲቻል ሆኖ የተዋቀረ ትምህርት ቤት ቢከፈት ሊረዳ ይችል ይሆናል:: ሆኖም የመምህራን እጥረት ችግር መንስኤው የመሰናዶ ትምህርት ቤት አለመኖር ሳይሆን ሌሎች አያሌ ችግሮች ስለሆነ ሌላ አማራጭ ከሌለ ሊከፈት ይችል ይሆናል:: ለነገሩ በዕደማርያምን የሚመስል ት/ቤት በዚህ ዘመን ለመክፈት አስቸጋሪ ሳይሆን አይቀርም::

ጠ/ መደምደሚያ

በዚህ አጭር ቅኝት ስለበዕደማርያም ት/ቤት ታሪክና ክንዋኔ ዎቹ ቀንጨብ ቀንጨብ በማድረግ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ይህ ጽሑፍ ስለመሰናደው ትምህርት ቤት ትኩረትን ለመሳብ የተዘጋጀ እንጂ በቂ ዘገባ ለማቅረብ የታቀደ ባለመሆኑ የአመሠራረቱን የክንዋኔውንና በመጨረሻም የተዘጋበትን ታሪክ ሙሉ በሙሉ ያካተተ አይደለም፡፡ስለዚህ አንባቢያች በዚህ መልኩ እንዲጠቁበት እንጋብዛለን፡፡

ሠ/ የግርጌ ማስታወሻዎች

[1] Ray T. Wilcox, Megletcha: A Magazine for Teachers Vol. 11 No. III "The Ethiopian-Laboratory School: Achievements and Prospects"

[2] Ibid

[3] Ibid

[4] Ibid

[5] Ibid

[6] UNESCO, Training of Secondary School Education, HSIU, Paris, May 1971, p.3.

[7] Task Force 11, Education Sector Review "Teacher Education Final Report "A.A. July 8, 1972.

[8] ትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መምህራን ትምህርትና ሥልጠና ጥናታዊ ግምገማ አዲስ አበባ፣ 1983፣ ገጽ 67.

[9] Ibid

10 ዓቢይ ክፍሌ /ዶ/ር/፣ በአ.አ.ዩ የ2ኛ ደረጃ መምህራን ትምህርት ያለበት ሁኔታ ደብዳቤ ቁጥር 80.6/3641/79 መጋቢት 10 ቀን 1979 ለትምህርት ሚኒስቴር የተፃፈ።

11 የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን፣ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠናና አደረጃጀት የወደፊት አቅጣጫ፣ አ.አ ነሐሴ 9 1980 ከገጽ 1 - 35.